የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶፰
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No. 58
ADDIS ABABA 31st July, 2025

**<u>ማውጫ</u>**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፫ / ፪ሺ፲፯
የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ ………………………………………..ገጽ ፲፰ሺ፱፻፹፱

**<u>Content</u>**

Proclamation No. 1383/2025
Solid Waste Management and Disposal Proclamation ……...............................Page 18989

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፫ / ፪ሺ፲፯

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ

›

ደረቅ ቆሻሻ በአካባቢ ሥነ-ምህዳር እና በሰዎች ደኅንነትና ጤና ላይ እያደረሰ ያለው ጉዳት ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ በመሆኑ፤

ደረቅ ቆሻሻ በአካባቢ እና በሰዎች ደህንነትና ጤና ላይ እያስከተለ ያለውን ተፅእኖ እና ጉዳት ለመከላከልና ለመቆጣጠር ውጤታማ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አጓጓዝ፣ አከመቻቸት፣ መልሶ መጠቀም፣ መልሶ ዑደት እና አወጋገድ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

## PROCLAMATION NO 1383 / 2025

## FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA SOLID WASTE MANAGEMENT AND DISPOSAL PROCLAMATION

**WHEREAS**, the environmental and public health risks posed by solid waste are steadily increasing over time;

**WHEREAS**, it is essential to develop an efficient system for the collection, transportation, storage, reuse, recycling, and disposal of solid waste to mitigate the growing impact of solid waste on the environment and human health and safety;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

https://ethiodata.et/

የተቀናጀ እና ዘላቂነት ያለው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ሥርዓት ለመዘርጋት የኅብረተሰብ እና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎን ማሳደግ እና በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አገልግሎት የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች፣ ማህበራት፣ የግሉ ዘርፍና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና ኃላፊነትን ብሎም ዘርፉ የሚመራበትን ሥርዓት በህግ መወሰን በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፫/፪ሺ፲፯” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **“ደረቅ ቆሻሻ”** ማለት የማይፈለግ ተብሎ የተጣለ ማንኛውም ፈሳሽ ያልሆነ ወይም ነፋሽ ያልሆነ ቆሻሻ ነው፤

**WHEREAS**, to build an integrated and sustainable solid waste management and disposal system, it is essential to enhance the involvement of the community and stakeholders, ensure the active participation and accountability of enterprises, associations, the private sector, and others engaged in waste management services, and establish a legally governed framework for the sector;

**NOW, THEREFORE**, In accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Solid Waste Management and Disposal Proclamation No.1383/ 2025".

**2. Definition**

In this Proclamation unless the context otherwise requires:

1/ **“Solid Waste”** means anything that is neither liquid nor gas and is discarded as unwanted;

https://ethiodata.et/

፪/ **"የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ"** ማለት ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ መቀነስ፣ በፈርጅ መለየትና መሰብሰብ፣ ማጓጓዝ፣ ማከም፣ መልሶ መጠቀም፣ መልሶ ዑደት ማድረግ እና አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ማስወገድ ነው፤

፫/ **"የመንገድ ፅዳት"** ማለት የተሽከርካሪ እና እግረኛ መንገድን፣ የመንገድ አካፋይን፣ ተሸጋጋሪ ድልድይን፣ የጎርፍ መዉረጃ ቦይን፣ የጉድፍ ማጠራቀሚያዎች፣ እና የመንገድ ዳር ልዩ ልዩ ምሰሶዎችን ማፅዳት ማለት ነዉ፤

፬/ **"ጉድፍ"** ማለት ደረቅ ቆሻሻ ሆኖ በሰዎች የሚመነጩ የሲጋራ ቁርጥራጭ፣ የሶፍት ወረቀት፣ የትራንስፖርት ደረሰኝ፣ የተንቀሳቃሽ ስልክ ካርድ፣ የፈጣን ምግቦች መጠቅለያ ወይም የመሳሰሉትን የሚያጠቃልል ነው፤

፭/ **"መልሶ መጠቀም"** ማለት ከደረቅ ቆሻሻ ውስጥ ጠቃሚ ዕቃዎችን በማውጣት ለተሰሩበት አላማ በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉበት ማንኛውም አሰራር ነው፤

፮/ **"መልሶ ዑደት ማድረግ"** ማለት ከደረቅ ቆሻሻ ውስጥ ጠቃሚ ቁሶችን በመለየትና ወደ ጥሬ እቃ በመቀየር ለቀድሞ አገልግሎታቸው ወይም ለሌላ አገልግሎት ማዋል ነው፤

2/ **"Solid Waste Management and Disposal"** means reducing, segregating and collecting, transporting, treating, reusing, recycling, and disposing solid waste from the source;

3/ **"Road Side Cleaning"** means cleaning pedestrian roads and road divides, pedestrian overpass drainages, litter bins, removing illegal adverts on light posts;

4/ **"Litter"** means any solid waste generated by humans which include cigarette butts, soft papers, transport tickets, fast food packaging or other like materials;

5/ **"Reuse"** means any operation by which products or components that are not waste are used again for the same purpose for which they were conceived;

6/ **"Recycle"** means separating and reprocessing of valuable materials from solid waste and turning them into raw materials for their previous use or other use;

https://ethiodata.et/

፯/ **"የቅብብሎሽ ማቢያ"** ማለት ወደ ማስወገጃ ቦታ ከመወሰዱ በፊት ደረቅ ቆሻሻን በጊዜያዊነት ለማከማቸት፣ በየፈርጁ ለመለየት፣ መልሶ ለመጠቀም እና መልሶ ዑደት ለማድረግ የተለየ ቦታ ነው፤

፰/ **"የማስወገጃ ቦታ"** ማለት ጥቅም የማይሰጥ የደረቅ ቆሻሻ በሰዉ እና በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዳያስከትል የሚወገድበት ቦታ ነዉ፤

፱/ **"ፕላስቲክ"** ማለት በዋናነት ከፔትሮኬሚካል የተሰራ፣ ለስላሳ እና የማይበሰብስ የፖሊመር ይዘት ያለው ምርት ነው፤

፲/ **"የፕላስቲክ ከረጢት"** ማለት አነስተኛ ጥግግት ያለው፣ በቀላሉ በስብሶ ከአፈር ጋር የማይዋሃድ እና ሌሎች ምርቶችን ለመያዝ የሚያገለግል ፕላስቲክ ነው፤

፲፩/ **"አንድ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክ"** ማለት መልሶ ጥቅም ላይ የማይውል ወይም መልሶ ዑደት የማይደረግ እና አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ ውሎ ቀጥታ የሚወገድ የፕላስቲክ ምርት ነው፤

፲፪/ **"የማሸጊያ ፕላስቲክ"** ማለት እቃዎችን ከብክለት ለመከላከል ወይም ከሌላ ነገር ጋር እንዳይቀላቀል ለማድረግ በእቃው አምራች ጥቅም ላይ የሚውል ከፕላስቲክ የሚዘጋጅ መጠቅለያ ወይም መያዣ ነው፤

፲፫/ **"አምራች"** ማለት በራሱ የንግድ ምልክት ምርት የሚያመርት ወይም ምርቱን ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባ ሰው ነው፡፡

7/ **"Transfer center"** means a separate place for temporary storage, sorting, reuse and recycling of solid waste before it is taken to a disposal site;

8/ **"Disposal Site"** means a place to dispose any useless solid waste in a manner that will not cause any harm to human and the environment;

9/ **"Plastic"** means a soft and non-degradable polymer-based material made primarily from petrochemicals;

10/ **" Plastic Bag"** means a low-density, non-biodegradable and a plastic used to contain other products;

11/ **" Single-Use Plastic"** means a plastic product that is not reused or recycled and used only once and is disposed of directly once used;

12/ **"Plastic Packaging"** means a plastic wrap or container used by the manufacturer of the product to protect the product from contamination or to keep it from mixing with other materials;

13/ **"Producer"** means a person who manufactures or imports a product under his own trademark;

https://ethiodata.et/

፲፬/ **"የተራዘመ የአምራቾች ኃላፊነት"** ማለት አምራቾች ለሚያመርቱት ምርት እስከ ድህረ-ሸማቾች የምርት የሕይወት ዑደት ደረጃ የሚራዘምበት ኃላፊነት ነው፤

፲፭/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯ መሰረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፮/ **"ከተማ"** ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ከተማ ተብሎ የተሰየመ ከተማ ነው፤

፲፯/ **"የከተማ አስተዳደር"** ማለት በከተሞች ውስጥ አስተዳደራዊ ወይም ማዘጋጃ ቤታዊ ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን እንዲሰጥ የተቋቋመና ራሱን የቻለ አስተዳደራዊ አካል ነው፤

፲፰/ **"የገጠር ቀበሌ"** ማለት በከተማ አስተዳደር ያልታቀፉ ቀበሌዎች ያጠቃልላል፤

፲፱/ **"ተቋም"** ማለት መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን ያጠቃልላል፤

፳/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፩/ **"ባለሥልጣን"** ማለት የፌደራል የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤

14/ **"Extended Producer Responsibilit"** means the responsibility of a producer for the product it produces, extending to the post-consumer stage of the product life cycle;

15/ **"Region"** means any region established according to Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and, includes the Addis Ababa and Dire Dawa City administrations;

16/ **"City"** means a municipality that has been constituted or designated as a city by a legally authorized body;

17/ **"City administration"** means an independent administrative body established to provide administrative or municipal administration services or other services;

18/ **"Rural Kebele"** mean a kebele that is not under city administration;

19/ **"Institution"** means any governmental or non-governmental institution;

20/ **"Person"** means any natural person or juridical person;

21/ **"Authority"** means the Federal Environmental Protection Authority;

https://ethiodata.et/

፳፪/ በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ያካትታል፡፡

## ፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፺/፪ሺ፲ ላይ በተሸፈኑ አደገኛ ቆሻሻዎች እና ከኤሌክትሪክና ኤሌክትሮኒክ ቆሻሻዎች በስተቀር በመላ ሀገሪቱ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ፬. መርሆዎች

ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የሚከተሉትን መሰረታዊ መርሆዎች መከተል ይኖርበታል፡-

፩/ ቆሻሻን ከምንጩ መቀነስ፣ መልሶ መጠቀም፣ መልሶ ዑደት ማድረግ እና በአግባቡ ማስወገድ፤

፪/ የህብረተሰብ ተሳትፎ ማሳደግ፤

፫/ የበከለን ማስከፈል።

# ክፍል ሁለት

# ስለደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ

## ፭. የተራዘመ የአምራቾች ኃላፊነት

፩/ የፕላስቲክ ምርት አምራቾች የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉባቸው፡-

ሀ) የፕላስቲክ ምርት ሲያመርቱ በአካባቢ ላይ አነስተኛ ተፅዕኖ ያላቸው የምርት ንድፎችን መከተል፤

ለ) በአመራረት ሂደት ሊከሰት የሚችለውን የፕላስቲክ ምርት ቆሻሻ የመቀነስ፤

22/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of application

This Proclamation shall apply to the management and disposal of solid waste throughout the country, except for hazardous wastes covered by Proclamation No. 1090/2018 and electrical and electronic waste.

## 4. Principles

The following fundamental principles shall guide all solid waste management and disposal practices:

1/ Reduction of waste generation from its source, reuse, recycle and disposal;

2/ Public participation;

3/ Polluter pay.

# PART TWO

# SOLID WASTE MANAGEMENT AND DISPOSAL

## 5. Extended Producers Responsibility

1/ Plastic product producers shall have the following responsibilities:

a) Adopt production designs that have minimal environmental impact of their plastic products;

b) Reduce plastic waste that may happen in the production process;

https://ethiodata.et/

ሐ) የፕላስቲክ ምርቱ የአገልግሎት ዘመን ሲያበቃ እንዲሰበሰብና ለዳግም ጥቅም ወይም መልሶ ዑደት ላይ ሊውል የሚችልበትን ሥርዓት የመፍጠር፣

መ) የፕላስቲክ ምርቱ የአገልግሎት ዘመኑ እንዳበቃ የሚሰበሰብበት፣ መልሶ ጥቅም ላይ እና ዑደት ላይ ለመዋል የሚያስፍለገውን ወጪ የመሸፈን።

፩/ የምግብ፣ የመጠጥ፣ የንጽህና መጠበቂያና የመዋቢያ ምርቶችን በጠርሙስ ወይም በቆርቆሮ ጣሳ ወይም በፕላስቲክ መያዣ የሚያመርቱ፣ የሚያስመጡ፣ የሚያከፋፍሉ ሰዎች ጠርሙሱ ወይም የቆርቆሮ ጣሳው ወይም የፕላስቲክ መያዣው የአገልግሎት ዘመኑ እንዳበቃ መልሶ የሚወሰድበትን ወይም እንዲወሰድ የሚያስደርግበትንና መልሶ ዑደት ወይም መልሶ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዘዴ የመዘርጋትና የመተግበር ግዴታ አለበት፡፡

## ፮. ደረቅ ቆሻሻ ስለመሰብሰብ

፩/ ከባለሥልጣኑ በሚሰጥ ፈቃድ ለጥሬ ምርትነት ካልሆነ በስተቀር ደረቅ ቆሻሻን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው።

፪/ ማንኛውም በደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ስራ ለመሰማራት የሚፈልግ ሰው በቅድሚያ ከሚመለከተው የከተማ አስተዳደር የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት አለበት፡፡

c) Ensure that the plastic product is collected at the end of its term of service for reuse or recycling;

d) Cover the cost of collecting, reusing and recycling their plastic products at the end of their term of service.

2/ The manufacturer, importer, whole seller and retailer of food, drink, hygiene protection and sanitary products with glass containers, tin cans and plastic bottles shall develop and implement a system that enables it to collect and recycle on its own or through other persons, used glass containers, tin cans and plastic bottles.

## 6. Collection of solid waste

1/ The importation of solid waste is prohibited, except for raw materials that have received approval from the authority.

2/ Any person intending to engage in the transportation of solid waste shall obtain a competency certificate from the relevant city administration.

https://ethiodata.et/

፫/ ማንኛውም ሰው ከመኖሪያ ቤቱ፣ ከአገልግሎት መስጫ ወይም ማምረቻ ተቋሙ የሚመነጭን ደረቅ ቆሻሻ በየፈርጁ መለየት፣ አመቺ በሆነ ቦታ በጊዜያዊነት ማከማቸትና ፈቃድ ለተሰጣቸው ቆሻሻ ሰብሳቢዎች ማስተላለፍ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ደረቅ ቆሻሻ ሰብሳቢዎች በማይኖሩበት አካባቢ የሚኖር ሰዉ ደረቅ ቆሻሻን ጊዜያዊ ማከማቻ ቦታ የማድረስ ኃላፊነት አለበት፡፡

፭/ ደረቅ ቆሻሻ በከተማ አስተዳደሮች በሚዘጋጁ የህዝብ የጋራ መገልገያ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች በጊዜያዊነት መከማቸ አለበት፡፡

፮/ የከተማ አስተዳደሮች የጉድፍ ማጠራቀሚያ ወይም በገንዳ የተጠራቀመ ቆሻሻ በተቀመጠለት ጊዜ የማንሳት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፯/ ማንኛውም ሰው የሞቱ እንስሳትን ለእነዚህ አይነት ቆሻሻዎች ተብሎ በተለየ ቦታ በጊዜያዊነት ማስቀመጥ አለበት።

## ፯. <u>የደረቅ ቆሻሻ ቅብብሎሽ ጣቢያ</u>

፩/ ማንኛውም የከተማ አስተዳደር እንደአስፈላጊነቱ የደረቅ ቆሻሻ የቅብብሎሽ ጣቢያ ማዘጋጀት አለበት፡፡

3/ Every individual shall be responsible for segregating, temporarily storing, and transferring solid waste from their households, service establishments, or manufacturing facilities to authorized collectors.

4/ Notwithstanding with Sub-Article (3) of this Article, individuals residing in areas without solid waste collection services shall be responsible for transporting their solid waste to designated temporary storage sites.

5/ Solid waste shall be temporarily stored in communal waste containers provided by the city administration.

6/ City administrations shall have the responsibility for the timely removal of solid waste from litter bins and containers.

7/ Each individual shall temporarily store deceased animals in a designated area specifically set aside for such materials.

## 7. <u>Solid waste transfer station</u>

1/ Each city administration shall set up a solid waste transfer station as deemed necessary.

https://ethiodata.et/

፪/ በከተማ ውስጥ የሚዘጋጅ ማንኛውም የቅብብሎሽ ጣቢያ የአካባቢውን ህብረተሰብ በማሳተፍ እና የህብረተሰቡን ፍላጎት መነሻ ማድረግ መዘጋጀት አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚዘጋጅ የቅብብሎሽ ጣቢያ በአካባቢ እና ማህበረሰብ ላይ ጉዳት የማያደርስ ስለመሆኑ በሚመለከተው አካል ተረጋግጦ መዘጋጀት አለበት፡፡

**፰. <u>ደረቅ ቆሻሻን መልሶ ስለመጠቀም፣ መልሶ ውደት ማድረግ እና ማስወገድ</u>**

፩/ ደረቅ ቆሻሻን መልሶ መጠቀም፣ መልሶ ዑደት ማድረግ እና ማስወገድ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ፣ የጤና እና ማህበራዊ ጠቀሜታ ባለው መንገድ እና ለህብረተሰቡ ፍላጎት ቅድሚያ በመስጠት መከናወን አለበት።

፪/ የደረቅ ቆሻሻን መልሶ መጠቀም፣ መልሶ ዑደት እና ማስወገድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ወይም ከክልል የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት አለበት፡፡

**፱. <u>የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው ለዚህ ተብሎ ከተዘጋጀ ቦታ ውጪ ደረቅ ቆሻሻን ማስወገድ አይችልም፡፡

2/ Each city administration shall have the responsibility to conduct public consultation before establishing any solid waste transfer station.

3/ The transfer station established under Sub-article (1) of this Article shall be certified by the relevant authority to confirm that it poses no harm to the environment and the community.

**8. <u>Reuse, recycle and disposal of solid waste</u>**

1/ The reuse, recycling, and disposal of solid waste shall be carried out in a manner that delivers economic, environmental, health, and social benefits, and aligns with the needs and priorities of the community.

2/ Any person intending to engage in the reuse, recycling, or disposal of solid waste shall obtain a competence certificate from the authority or the regional environmental protection office.

**9. <u>Solid Waste Disposal</u>**

1/ No person shall dispose of solid waste outside the designated area.

https://ethiodata.et/

፪/ ማንኛውም ሰው በከተማዎች አካባቢ በህዝብ ወይም በግል ይዞታ ላይ ደረቅ ቆሻሻን በማቃጠል ማስወገድ አይችልም፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የተደነገገው ቢኖርም ደረቅ ቆሻሻን ከሚመለከተው የከተማ አስተዳደር ፈቃድ ባገኘ የማቃጠያ መሳሪያ ለዚሁ በተፈቀደ ስፍራ እና ሁኔታ ማስወገድ ይቻላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ስለቆሻሻ አወጋገድ የተደነገገዉ አጠቃላይ ሁኔታ አግባብ ባላቸው ህጎች ስለደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ለሌሎች ተቋማት የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነት የሚያስቀር አይሆንም፡፡

## ክፍል ሶስት
## የልዩ ልዩ ደረቅ ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ

**፲. የመኖሪያ፣ የአገልግሎት መስጫ ወይም የማምረቻ ተቋማት የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ**

፩/ ማንኛውም ሰው ከመኖሪያ ቤት ይዞታው ድንበር አንስቶ እስከ ሀያ ሜትር ባለው ርቀት ውስጥ ደረቅ ቆሻሻን የማጽዳት ሃላፊነት አለበት፡፡

2/ No person shall dispose of solid waste by burning it in public or private spaces in cities.

3/ Notwithstanding with Sub-Article (2) of this Article, solid waste may be disposed of using an incinerator authorized by the relevant city administration, at a location and under conditions approved for this purpose.

4/ The general provisions set forth in this Article concerning waste disposal shall be without prejudice to the mandates, duties, and responsibilities conferred upon other institutions under applicable laws in relation to waste disposal.

## PART THREE
## MANAGEMENT AND DISPOSAL OF DIFFERENT TYPES OF SOLID WASTES

**10. Solid waste management and disposal by households, service institutions, or manufacturing entities.**

1/ Each person shall clean its surroundings and prevent littering within a radius of twenty meters from its household.

https://ethiodata.et/

፪/ ማንኛውም የአገልግሎት መስጫ ወይም የንግድ ተቋም ከይዞታው ድንበር አንስቶ ቢያንስ እስከ ሀምሳ ሜትር ባለው ርቀት ውስጥ ደረቅ ቆሻሻን የማጽዳት ሃላፊነት አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም የአገልግሎት መስጫ ወይም የንግድ ተቋም በየቆሻሻ ፈርጁ ተለይተው ምልክት የተደረገባቸዉ የጉድፍ ማጠራቀሚያዎች አመቺ በሆነ ቦታ ማስቀመጥ አለበት፡፡

**፲፩. <u>የግንባታና የፍርስራሽ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ</u>**

፩/ የግንባታ ፈቃድ የሚሰጠው የስራ ተቋራጩ የግንባታ ፍርስራሽ ወይም ተቆፍሮ የወጣ አፈር አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ እንደሚያስወግድ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የከተማ መኖሪያ ቤት ወይም ሌላ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት የከተማ አስተዳደር አካባቢያዊ ተቀባይነት ያለው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ በቂ ዝግጅት መኖሩን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ የግንባታ ፍርስራሽ ወይም ተቆፍሮ የወጣ አፈር በማስወገድ ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ወይም አግባብነት ካለው የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት የብቃት ማረጋገጫ ማግኘት አለበት፡፡

2/ Every service or commercial institution shall clean and its surroundings from littering within a radius of fifty meters from its premises.

3/ Every service or commercial establishment shall provide waste bins labeled according to each waste category in a convenient location.

**11. <u>Construction Debris and Demolition Wastes</u>**

1/ Construction permits shall only be granted when it is demonstrated that the contractor can manage the disposal of construction debris or excavated earth in an environmentally sound manner.

2/ Notwithstanding with Sub-Article (1) of this Article, city administrations shall ensure that proper provisions for environmentally sound solid waste management are in place before starting the construction of residential or other buildings.

3/ Any person intending engage in the disposal of construction debris or demolition waste shall obtain a permit from the authority or regional environmental protection office.

https://ethiodata.et/

፬/ በጊዜያዊነት የግንባታና የፍርስራሽ ቆሻሻ እንዲያከማች የተፈቀደለት ሰው የተከማቸበት ቦታ በተፈቀደለት ጊዜ ውስጥ ወደ ቀድሞው ሁኔታ መመለስ አለበት፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ቆሻሻው የመነጨበት ቅጥር ግቢ ባለቤት እና ግንባታውን የሚያካሂደው ሰው ፡-

ሀ) የግንባታ ፍርስራሽ ቆሻሻው እስከሚወገድ ድረስ በግንባታው ቅጥር ግቢ ውስጥ መቀመጡን፤

ለ) የግንባታና ፍርስራሽ ቆሻሻ ጊዜያዊ ክምችት የሰዎችን እንቅስቃሴ የማይገታና ጉዳት የማያስከትል መሆኑን፤

ሐ) ከመነጨው የግንባታና ፍርስራሽ ቆሻሻ የሚጠቅመውን ከማይጠቅመው ለይቶ በጊዜያዊነት መከማቸቱን፤

መ) የመነጨው ቆሻሻ ለማስወገድ ፈቃድ ላለው አካል ብቻ መተላለፉን፤

ሠ) ከከተማ አስተዳደሩ በሚሰጥ ትእዛዝ መሰረት እንደአስፈላጊነቱ የግንባታ ፍርስራሽ ቆሻሻን በአግባቡ ለመያዝ የሚያስችል ግንባታ መከናወኑን፤ ማረጋገጥ አለበት፡፡

4/ Any individual authorized to temporarily store construction debris and demolition waste shall restore the site to its original condition once the time limit expires.

5/ The Authority or Regional Environmental Protection office shall regulate the owner or occupant of premises where building waste is generated, as well as the individual conducting activities that lead to the generation of such waste, ensuring that:

a) The construction debris shall be kept on the premises where it was generated until it is disposed of;

b) The temporary storage of the construction debris shall not obstruct the movement of people or cause any harm;

c) The construction debris shall be segregated and stored temporarily;

d) The waste shall be transferred to authorized bodies for disposal;

e) Any structure required to contain the waste shall be provided in accordance with instructions from the city administration.

https://ethiodata.et/

**፲፪. <u>ጠርሙስ፣ ጣሳ፣ የታሸገ ውኃ መያዣ ፕላስቲክ</u>**

፩/ የከተማ አስተዳደሮች ቆሻሻ ጠርሙስ፣ የቆርቆሮ ጣሳ ወይም ፕላስቲክ መያዣ በጊዜያዊነት የሚከማችበት ቦታ መመደቡንና ክምችቱም በየወቅቱ መነሳቱን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

፪/ መያዥ ጠርሙስ፣ የቆርቆሮ ጣሳ እና የፕላስቲክ ንድፎች የምርቶቹን መልሶ መጠቀምና መልሶ ዑደት ማድረግን ታሳቢ ያደረገ መሆን አለበት፡፡

**፲፫. <u>ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክ</u>**

፩/ ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክ ማምረት፣ ለገበያ ማቅረብ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ መሸጥ፣ ማከማቸት ወይም መጠቀም የተከለከለ ነው።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት አገር ውስጥ በተመረተ፣ ወደ አገር ውስጥ በገባ፣ ለመግባት በሂደት ላይ ባለ ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው ልዩ ሁኔታ ተፈጻሚ የሚሆነው ይህ አዋጅ ስራ ላይ ከዋለበት ገዜ ጀምሮ ለስድስት ወር ብቻ ነው።

**12. <u>Bottles, cans, bottled water plastic</u>**

1/ City administrations shall ensure that waste bottles, tin cans, and plastic containers are temporarily stored in a designated area and that they are collected and removed periodically.

2/ The design of glass containers, tin The design of glass containers, tin cans, and plastic bottles shall consider the potential for reuse and recyclability of the products.

**13. <u>Single-use plastic</u>**

1/ The production, placing into the market, importation, storage, sale, or use of any single-use plastic is prohibited.

2/ The provision in Sub-Article (1) of this Article shall not apply to single-use plastic manufactured domestically, imported into the country, or in the process of being imported before the coming into force of this proclamation.

3/ The special condition outlined in Sub-Article (2) of this Article shall be valid only for six months from the effective date of this Proclamation.

https://ethiodata.et/

፬/ ባለስልጣኑ ወይም የክልል የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ደንጋጌዎች አፈጻፀም ላይ ቁጥጥር ያደርጋል፣ ጥሰት ሲኖር ተገቢው የእርምት እርምጃ ይወስዳል።

**፲፬. ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክን በልዩ ሁኔታ ስለመፍቀድ**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ ፕላስቲኮች እንዲመረቱ፣ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ወይም ጥቅም ላይ እንዲውሉ በመመሪያ ሊወስን ይችላል።

፪/ ባለስልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በመመሪያ ሊወስን የሚችለው ፕላስቲክ ማሸጊያው በቀላሉ በሌላ ምርት የማይተካ መሆኑ እና ፕላስቲኩ ለዚህ ዓላማ ብቻ የሚውል መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

፫/ በዚህ አዋጅ ላይ በተደነገገው ልዩ ሁኔታ መሰረት አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክ የሚያመርት፣ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባ፣ የሚያከማች፣ የሚያሰራጭ፣ ወይም የሚጠቀም ሰው ፕላስቲኩ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ እና የፕላስቲኩ ቆሻሻ በአግባቡ የሚያዝበት ወይም የሚወገድበትን ሥርዓት መዘርጋት አለበት።

4/ The Authority or the Regional environmental protection office shall regulate the enforcement of the provisions of this Proclamation related to single-use plastic and take appropriate corrective measures in the event of violations.

**14. Authorization of the use of single-use plastic under special conditions**

1/ Notwithstanding with Article 13 of this Proclamation, the authority shall issue a directive to regulate the production, import, or use of single-use plastics under special conditions.

2/ The Authority may issue a directive under Sub-Article (1) of this Article when it is determined that the plastic packaging cannot be easily substituted with another product and is used solely for this purpose.

3/ Any person who manufactures, imports, stores, distributes, or uses single-use plastic under the special conditions outlined in this proclamation shall ensure that the plastic complies with the standards and establish a system for the proper handling or disposal of the plastic waste.

https://ethiodata.et/

፬/ በዚህ አዋጅ ላይ በተደነገገው ልዩ ሁኔታ መሰረት አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክ የሚያመርት ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገባ ሰው በፕላስቲክ ማሸጊያው ላይ ስለምርቱ እና ማሸጊያ ፕላስቲኩ ገላጭ ፅሑፍ መቀመጡን ማረጋገጥ አለበት።

፭/ ይህ አዋጅ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክ ማምረት ላይ የተሰማራ አምራች ወይም አስመጪ ይህ አዋጅ ስራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ባለው ስድስት ወር ውስጥ በዚህ አንቀጽ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

፮/ በዚህ አንቀፅ ላይ የተቀመጡት ልዩ ሁኔታዎች የፕላስቲክ ከረጢት ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም።

## ፲፭. <u>ጉድፍ እና የጉድፍ ማጠራቀሚያ አያያዝና አጠቃቀም</u>

፩/ ሁሉም የከተማ አስተዳደሮች የጉድፍ ማጠራቀምያ ዕቃዎችን በተገቢ ቦታዎች ላይ የማስቀመጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው የጉድፍ ቆሻሻዎችን በጉድፍ ማጠራቀሚያ ውስጥ የመጣል ግዴታ አለበት፡፡

፫/ ሁሉም የከተማ አስተዳደሮች የጉድፍ ማጠራቀሚያ ወይም በገንዳ የተጠራቀመ ቆሻሻ በተቀመጠለት ጊዜ የማንሳት ኃላፊነት አለባቸው::

4/ Any person who manufactures or imports single-use plastic under the special conditions specified in this proclamation shall ensure that the product description and plastic packaging details are clearly labeled on the packaging.

5/ Any importer or manufacturer engaged in the production of single-use plastic before the entry into force of this Proclamation shall comply with the requirements outlined in the proclamation within six months.

6/ The exceptions outlined under this Article do not apply to plastic bag.

## 15. <u>Management of litter and handling and use of Litter bin</u>

1/ All city administrations shall have the responsibility to place litter bins in appropriate places.

2/ Every person shall have the responsibility to dispose litter in litter bin.

3/ All city administrations shall have the responsibility to dispose waste collected in litter bin or waste storage containers.

https://ethiodata.et/

## ክፍል አራት

## የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ መሳሪያዎች እና ቦታዎች

### ፲፮. የደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎች

፩/ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር ለደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎችና መሳሪያዎችን በስራ ላይ ማዋል አለበት፡፡

፪/ የደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ወይም መሳሪያ በስራ ላይ ከመዋሉ አስቀድሞ አገልግሎት የመስጠት ብቃቱ በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል በቅድሚያ መረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ አግባብ ባለው ሕግ የተወሰነው የተሽከርካሪ ክብደትና መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዣ ተሽከርካሪ ሾፌሮችንና የመሳሪያ አንቀሳቃሾችን ክህሎት ለመወሰን እና ከልክ ያለፈ የደረቅ ቆሻሻ ጭነትን ለመከላከል የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ማውጣት አለበት፡፡

### ፲፯. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች

፩/ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር አግባብነት ያለው የአካባቢ ደረጃ በመከተል የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንዲገነባና አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ አለበት::

## PART FOUR

## SOLID WASTE DISPOSAL SITES AND MACHINERY

### 16. Vehicles and Tools for Solid Waste Transportation

1/ Every city administration shall have the responsibility for ensuring the deployment of appropriate vehicles and equipment for solid waste transportation.

2/ Any vehicle or equipment intended for solid waste transport shall be verified for suitability by a legally authorized entity before being put into use.

3/ Without affecting the existing legal standards on vehicle weight and size, city administrations shall establish criteria for assessing the qualifications of drivers and equipment operators, as well as measures to prevent overloading of solid waste.

### 17. Sanitary Landfill

1/ Every city administration shall, in conformity with the relevant environmental standard, ensure that sanitary landfill is constructed and properly used.

https://ethiodata.et/

፪/ ከከተማው አስተዳደር ክልል ውጭ የሚገነባ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የተቀባዩን የከተማ አስተዳደር ወይም ከሚመለከተው አካል ስምምነት ማግኘት አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ በሚመለከተው አካል በተቀመጠው መስፈርት መሰረት መዘጋጀት እና አስፈላጊ መሰረተ ልማቶችን ያሟላ መሆን አለበት፡፡

## ፲፰. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ አስተዳደር

፩/ ማንም ሰው የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታን ከታለመለት አላማ ውጭ መጠቀም አይችልም፡፡

፪/ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች በሰው ሀይልና በግብዓት የተሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፫/ እያንዳንዱ የከተማ አስተዳደር በደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች የሚወገድ የቆሻሻ መጠንና አይነት መረጃ መያዝ አለበት፡፡

2/ Before the commencement of construction of any sanitary landfills outside the boundary of a city administration, the city administration shall obtain consent from the relevant authority or from the recipient city administration.

3/ Any solid waste disposal site must be prepared according to the criteria set by the relevant body and equipped with the necessary infrastructure.

## 18. Management of Sanitary Landfill

1/ No person shall utilize a sanitary landfill for any purpose other than its primary function.

2/ Every city administration shall ensure that sanitary landfills is furnished with adequate personnel and essential equipment necessary for its proper operation.

3/ Every city administration shall maintain systematic and periodic records indicating the classification and volume of waste deposited at solid waste disposal facilities.

https://ethiodata.et/

## ክፍል አምስት
## የአስፈፃሚ ወይም ሌሎች ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

### ፲፱. የከተማ አስተዳደር ግዴታ

በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የከተማ አስተዳደር፡-

፩/ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ መሰረተ ልማቶች በከተማ ፕላን በግልፅ ማመላከት፤

፪/ ዝቅተኛውን የአስተዳደር እርከኑንና የአካባቢውን ማህበረሰብ መነሻ ባደረገ አሳታፊ የአሰራር ዘዴ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ዕቅድ አዘጋጅቶ የመተግበር፤

፫/ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እና የአካባቢ መንከባከቢያ የግንዛቤ ማስፋፊያ መርሃ ግብር የማቀድና የማከናወን፤

፬/ ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ጉድለት ሊደርስ የሚችል ብክለትን መከላከል የሚያስችል ስራ መከናወኑን የማረጋገጥ፤

## PART FIVE
## POWERS AND DUTIES OF THE EXECUTIVE OR RELATED INSTITUTIONS

### 19. Obligations of City administration

Without prejudice to the other provisions of this Proclamation, every city administration shall have the following obligations:

1/ Expressly indicate the inclusion of solid waste management infrastructure within the urban development plan;

2/ To ensure active participation of the lowest administrative units and their respective local communities in the formulation and implementation of localized solid waste management plans;

3/ To plan and implement programs related to solid waste management, disposal, and public awareness on environmental protection and cleanliness;

4/ To take appropriate preventive measures against pollution resulting from improper handling of solid waste;

https://ethiodata.et/

፭/ የጉድፍ ማስቀመጫዎችን በመንገድ ዳር እና ህዝብ በሚያዘወትርባቸዉ ቦታዎች ማስቀመጥ፤ በየጊዜዉ መፅዳታቸዉን ማረጋገጥ፤

፮/ የመንገድ ፅዳት ሥርዓት የመዘርጋት፤

፯/ አካባቢን የሚያቆሽሹ የማስታወቂያ ሥራዎችን የመቆጣጠር፤

፰/ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ላይ ወቅታዊ የአካባቢ ኦዲት በማከናወን ሪፖርቱን ለባለሥልጣኑ ወይም ለክልል የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤቶች ማቅረብ፤

፱/ አግባብነት ያላቸው ወጪ ቆጣቢ እና ለአጠቃቀም ምቹ የሆኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝን የሚያግዙ ቴክኖሎጂዎች ሥራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ፤

፲/ በከተማዉ ዉስጥ የሚገኙ የወንዝ ዳርቻዎች፣ የገበያ ቦታ፣ የህዝብ ማዘዉተሪያ ቦታዎች፣ አረንጓዴ ስፍራዎች እና መሰል ቦታዎችን ማፅዳት እና ቆሻሻ እንዳይጣልባቸዉ የመቆጣጠር፤

፲፩/ ዘላቂነት ያለው የቆሻሻ አያያዝ ተግባራትን ማከናወኛ ፋይናንስ ምንጭና ሥርዓት መዘርጋት እና መኖሩን የማረጋገጥ፤

5/ To install litter bins along roadsides and in public spaces, and to ensure their regular maintenance and emptying;

6/ To establish a system for street and roadside cleaning;

7/ To regulate and control advertising activities that may contribute to environmental pollution;

8/ Conduct periodic environmental audit and submit the report the authority and Regional environmental protection office;

9/ To ensure the adoption of cost-effective, environmentally sound, and user-friendly technologies for solid waste management;

10/ To ensure that solid waste is not disposed of in areas such as riverbanks, market areas, public open spaces, green areas, or other environmentally sensitive locations, and to conduct regular monitoring thereof;

11/ To develop and implement a sustainable financing mechanism to support solid waste management initiatives;

https://ethiodata.et/

፲፪/ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ የሚያሳድግ የማበረታቻ ሥርዓት የመዘርጋት፣

፲፫/ ዓመታዊ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዘገባ ማዘጋጀት እና ለባለሥልጣኑ ወይም ለክልል የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት እና ለከተማ እና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ወይም ለክልል የከተማ እና መሰረተ ልማት መስሪያ ቤት የማቅረብ፣

፲፬/ ደረቅ ቆሻሻን መልሶ ለመጠቀም፣ መልሶ ዑደት በማድረግ እና በማስወገድ ስራ ላይ የሚሰማሩ ሰዎችን ለማበረታታት የሚያስችሉ እርምጃዎችን የመዉሰድ፣ ግዴታ አለበት፡፡

## ፳. <u>የገጠር ቀበሌ አስተዳደር ግዴታዎች</u>

፩/ ማንኛውም የገጠር ቀበሌ አስተዳደር ፡-

ሀ) በገጠር ቀበሌዎች የሚመነጭ የደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ መያዙንና መወገዱን የማረጋገጥ፣

12/ To establish incentive schemes that promote the private sector participation in solid waste management services;

13/ Compile and submit an annual report on integrated solid waste management and disposal activities to the competent authority or Regional Environmental Protection Office, as well as to the Ministry of Urban Development and Infrastructure or the corresponding Regional Urban and Infrastructure Development Office;

14/ To promote and support activities related to the reuse, recycling, and disposal of solid waste.

## 20. <u>Obligations of Rural Kebele Administration</u>

1/ Every rural kebele administration shall have the following responsibilities:

a) To ensure that solid waste generated within its jurisdiction is properly managed, handled, and disposed of in an environmentally sound manner;

ለ) የደረቅ ቆሻሻ ዝውውርን የመቆጣጠር፣ ግዴታ አለበት፡፡

b) To regulate the transportation of solid waste within its territorial bounds;

፪/ ለከተማ አስተዳደሮች በዚህ አዋጅ የተሰጡ ሀላፊነቶች እንደአስፈላጊነቱ ለገጠር ቀበሌ አስተዳደሮችም ይሰራሉ::

2/ Where applicable, all duties and responsibties conferred upon city administrations under this Proclamation shall likewise be deemed to apply to rural kebele administrations.

**፳፩. <u>በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የኢንተርፕራይዞች እና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ</u>**

**21. <u>Participation of the private sector and enterprises in the management and disposal of solid waste</u>**

፩/ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የሚሰማሩ የኢንተርፕራይዞች እና የግሉ ዘርፍ ከባለሥልጣኑ ወይም አግባብነት ካለው የክልል አካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ፈቃድ ማውጣትና ፍቃዳቸውን በየዓመቱ ማሳደስ አለባቸው፡፡

1/ Private sector entities and enterprises seeking to engage in solid waste management and disposal activities shall first obtain a certificate of competence from the Authority or the appropriate Regional Environmental Protection Office, and shall thereafter renew such certificate on an annual basis.

፪/ የከተማና የገጠር አስተዳደሮች እንደ አስፈላጊነቱ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አገልግሎቶችን በጥቅል ወይም በተናጠል ለግል ባለሀብቶች፣ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ወይም ኢንተርፕራይዞች ሊያስተላልፉ ይችላሉ፡፡

2/ City and rural kebele administrations may, where deemed appropriate, delegate all or part of their solid waste management and disposal responsibilities to private investors, non-governmental organizations, or other qualified enterprises.

https://ethiodata.et/

፫/ የከተማ አስተዳደሮች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ለሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞችና የግሉ ተቋማት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ አለባቸው፡፡

**፳፪. <u>የሙያ ደኅንነት፣ጤንነትና የሥራ አካባቢ</u>**

፩/ ማንኛውም በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ የተሰማራ ተቋም የሠራተኞችን ደኅንነትና ጤንነት በሚገባ ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል፡፡

፪/ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ወይም በሌሎች ህጎች ላይ የተደነገገው የሙያ ደኅንነት፣ ጤንነትና የሥራ አካባቢ መስፈርቶች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ላይ ለተሰማሩ ሰዎችም ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>
## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፳፫. <u>የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አገልግሎት ክፍያ</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው ለደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አገልግሎት ክፍያ የመፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

3/ City administrations shall extend the necessary support to private sector entities and enterprises seeking to engage in solid waste management operations.

**22. <u>Protection of Occupational Safety, Health, and Workplace environment</u>**

1/ Any facility engaged in solid waste management and disposal shall implement appropriate measures to ensure the adequate protection of the health and safety of their workers.

2/ The occupational health and safety standards set forth under the Labor Proclamation and other laws shall apply to all individuals engaged in solid waste management and disposal activities.

## <u>PART SIX</u>
## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

**23. <u>Solid Waste Management and Disposal Service Charge</u>**

1/ Every person shall have the obligation to pay the prescribed service fee for solid waste management and disposal service.

https://ethiodata.et/

፪/ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አገልግሎት ክፍያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

**፳፬. <u>አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>**

ባለስልጣኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ላይ ተፈጻሚ የሚሆን፣ የክልል የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በክልል ደረጃ ተፈጻሚ የሚሆን መመሪያ በማውጣት ይህን አዋጅ በመተላለፍ በሚፈፀሙ የሚከተሉት አስተዳደራዊ ጥፋቶች ላይ የሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃን እንደአካባቢ እና ነባራዊ ሁኔታው እያዩ ይወስናሉ፡-

፩/ ከጉድፍ መጣያ ቦታ ውጭ በመኪና መንገድ፣ በእግረኛ መንገድ፣ በፓርኮችና በመሳሰሉ ቦታዎች ጉድፎችን መጣል፤

፪/ ከባለስልጣኑ ወይም ከክልል የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ፍቃድ ሳያገኝ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ላይ መሰማራት፤

፫/ በዚህ አዋጅ ከተቀመጠው አግባብ ውጭ የደረቅ ቆሻሻን በማቃጠል ማስወገድ፤

2/ The Council of Ministers may issue Regulation governing the determination and administration of fees related to solid waste management and disposal service.

**24. <u>Administrative measures</u>**

The Authority shall issue directive applicable to the Addis Ababa and the Dire Dawa City Administration, and the Regional Environmental Protection Office shall issue directive applicable to the Region for the purpose of prescribing administrative measures to be taken in response to the commission of the following administrative offenses in violation of this Proclamation:

1/ Disposing of litter in driveways, sidewalks, parks, or similar public areas outside of designated waste receptacles;

2/ Undertaking solid waste management and disposal activities without first obtaining the required license from the authority or the relevant regional environmental protection office;

3/ Disposing of solid waste through open burning, except in circumstances expressly permitted under this Proclamation;

https://ethiodata.et/

፬/ በቆሻሻ ማሰባሰቢያ ማዕከል የተቀመጠ የቆሻሻ መያዣን ማውደም ወይም ጉዳት ማድረስ፤

፭/ ደረቅ ቆሻሻን ከተሽከርካሪ፣ ከመኖሪያ ቤት ወይም ከማንኛውም ቅጥር ግቢ አውጥቶ ወደ አልተፈቀደ ቦታ መወርወር፣ ማስቀመጥ ወይም ማከማቸት፤

፮/ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አጓጓዝ ላይ እክል መፍጠር፤

፯/ ሳያስፈቅድ አካባቢን የሚያቆሽሽ የማስታወቂያ ሥራ ማከናወን፤

፰/ የሞቱ እንስሳትን ለእነዚህ ተብለው ከተወሰኑ ቦታዎች ውጭ መጣል፤

፱/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፬ በልዩ ሁኔታ ከሚፈቀድ ለአንድ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክ በሚቃረን ሁኔታ ለአንድ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክ፡-

ሀ) መጠቀም ወይ ለመጠቀም ይዞ መገኘት፤

4/ Damaging, destroying, relocating, or causing loss to containers placed at solid waste collection centers;

5/ Illegally placing, throwing, or depositing solid waste from vehicles, residences, compounds, or premises onto roads or other public spaces not authorized for such use;

6/ Causing obstruction, interference, or impairment in the handling, collection, or transportation of solid waste;

7/ Conducting advertising activities that result in environmental pollution without prior authorization;

8/ Depositing, placing, or storing dead animals outside areas designated for such purposes;

9/ Subject to the special conditions set forth in this Proclamation for single-use plastics product:

a) Using or intending to use single-use plastic products;

https://ethiodata.et/

ለ) ማምረት ወይም ወደ ሃገር ውስጥ ማስገባት፣ ለገበያ ማቅረብ ወይም መሸጥ፣ ለንግድ ዓላማ ማከማቸት ወይም ይዞ መገኘት፤

፲/ ሌሎች በጥናት የሚለዩ መሰል ጥፋቶች።

**፳፭. <u>የወንጀል ተጠያቂነት</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው የፕላስቲክ ከረጢት፡-

ሀ) ከተጠቀመ ወይም ለመጠቀም ይዞ ከተገኘ ከሁለት ሺ ብር በማያንስና ከአምስት ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

ለ) ካመረተ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ ካስገባ፣ ለገበያ ካቀረበ ወይም ከሸጠ፣ ለንግድ አላማ ካከማቸ ወይም ይዞ ከተገኘ ከሀምሳ ሺ ብር በማያንስና ከሁለት መቶ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከአምስት አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን የወንጀል ድርጊቶች የፈጸመዉ ህጋዊ ሰውነት ያለዉ ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ የገንዘብ ቅጣቱ በንዑስ አንቀጹ የተመለከተዉን ሶስት እጥፍ ይሆናል፡፡

b) Manufacturing, importing, marketing, selling, storing, or possessing single-use plastic products for commercial purposes.

10/ Other related administrative. Violations.

**25. <u>Criminal liability</u>**

1/ Any individual who:

a) Uses or intends to use a plastic bag shall be subject to a fine of no less than two thousand birr and no more than five thousand birr;

b) Manufactures, imports, distributes, sells, stores, or possesses plastic bags for commercial purposes shall be subject to a fine of no less than fifty thousand birr and no more than two hundred thousand birr, along with a term of rigorous imprisonment not exceeding five years.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, if the offence is committed by an institution, the penalty to be imposed shall be three times the amount prescribed therein.

https://ethiodata.et/

፫/ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው የወንጀል ተጠያቂነት በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሰረት ሊወሰዱ የሚችሉ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የሚያስቀር አይሆንም።

3/ The criminal penalties outlined in this Article do not preclude the possibility of administrative actions being taken in accordance with this Proclamation and the directives issued pursuant to it.

## ፳፮. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 26. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The authority may issue directives for the implementation of this Proclamation and the regulation issued pursuant to this Proclamation.

## ፳፯. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

፩/ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፫/፩ሺ፱ሺ፺፱ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ደንብና መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 27. Repeals

1/ Solid Waste Management Proclamation No. 513/2007 is hereby by repealed.

2/ No law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, have effect on matters provided for in this Proclamation.

https://ethiodata.et/

**፳፰. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አፅቀ ስላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ፕሬዘዳንት**

**28. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 31st Day of July, 2025**

**TAYE ATSKE SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://ethiodata.et/